የሰበር መ/ቁ-18307

ጥቅምት 25 ቀን 1998

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/

መልስ ሰጭ፡- አቶ ተገኑ መሸሻ

የስራዎች አገልግሎት መስጠትን የሚመለከቱ ውሎች - ለሰራተኛው ስለሚገባው የደመወዝ መብት- ስራ ላልተሰራባቸው ቀናት ደመወዝ ስላለማግኘት- ስለ ስራ አለመኖር /በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ ስለሆነ ሰራተኛ/ ፡- የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2534፣ 2540፣ 2541/1/

መልስ ሰጭ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በቴክኒክ ዋና ክፍል ሀላፊ ሆኜ ስሰራ ከስራ ከመሰናበቴ በፊት ታግጄ በቆየሁበት ከታህሳስ 23 ቀን

1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ያለው ደመወዜ እንዲከፈለኝ በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መ/ሰጭ የጠየቀው ገንዘብ እንዲከፈለው ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ:- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል።

1. በድርጅት ስራ መሪና በድርጅቱ መካከል ያለ የስራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሄር ህጉ የስራ አገልግሎትን መስጠት ስለሚመለከቱ ውሎች ከቁጥር 25/2 እና ተከታታዮቹ በተደነገጉት ህጎች መሰረት ነው።
2. የስራ መሪ ደመወዝ ለተሰራ ስራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሰራ ስራ የሚከፈል አይደለም
3. የስራ መሪው አንድም የስራ አገለግሎት ባይሰጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሰሪው ስራ ሳይሰጠው በመቅረቱ ወይም እንዳይሰራ

በመካልከሉ የተነሳ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት ያለው ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሰራተኛው /የስራ መሪው/ ስራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሰሪው ሥራ ሳይሰጠው ወይም እንደይሰራ በከለከለው ጊዜ እንጂ ሠራተኛው ከስራና ከደመወዝ ታግዶ የስራ አገልግሎት ላልሰጠባቸው ጊዜያት አይደለም፡፡

የሠበር መ/ቁ.18307

ቀን 25 - 2 - 98

ዳኞች፡- አቶ መንበረ ፀሐይ ታደሠ

አቶ ፍስሃ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አቶ አሠግድ ጋሻው

አመልካች፡-ንብ ትራንስፖርት አክሲዮን ማኀበር

ተጠሪ፡- አቶ ተገኑ መሸሻ

ለዚህ የሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው።

በሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ ሲሆን አመልካቹ ተከሣሽ ነበር።

የተጠሪው የሥር ክሥ በድርጅቱ ውስጥ የቴክኒክ ዋና ክፍል ሀላፊ ሆኜ ስሠራ ከታህሣስ 23/94 ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራ ታግጄ ከቆየሁ በኂዋላ ሰኔ 5/95 የተፃፈ የሰንበት ደብዳቤ ተሠጥቶኛል ስለዚህ

ከታገድኩበት ጊዜ አንስቶ እስከተሠናበትኩበት ጊዜ ድረስ ያለው የ17 ወር ከ15 ቀን የተጣራ ደመወዜ 23,500 /ሃያ ሦስት ሺ.ህ አምስት መቶ ብር ወጭና ኪሣራ ተጨምሮ ይከፈለኝ የሚል ነው።

የሥር ተከሣሽ ማለትም ተጠሪው ቀርቦ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ በብይን ውድቅ የተደረገበት ቢሆንም ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሣሽ ከሥራ የተሠናበተው ድርጅቱን የሚጎዳ ተግባር የፈፀመ መሆኑን በመግለፅ ሥራ ላልሠራበት ጊዜ ደመወዜ ሊከፈለው እንደማይገባ ይከፈለው ቢባል እንኳ ከ3ወር ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በመግለፅ ተከራክሯል።

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከሣሽ የሥራ መሪ እንደመሆኑ በፍ/ህጉ ላይ የሥራ መሪን ከሥራ ስለማገድ የተደነገገ ድንጋጌ የለም፣ በድርጅቱ የውስጥ ደንብ ስለመኖሩና በውስጡ ደንቡ መሠረት ስለማገዱ አላስረዳም በመልስ የዘረዘራቸውን ተግባራት ከሣሽ ፈጽመዋል ቢባል እንኳ ከሥራና ከደመወዝ ለማገድ በቂ ምክንያቶች አይደሉም በፍ/ህ/ቁጥር 2574/1/ ሠራተኛው አገልግሎት ባይሠጥም ይህ የሆነው በአሠሪው ምክንያት ከሆነ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ አለበት፣ የ3ወር

ደመወዝ ብቻ ሊከፈላቸው ይገባል የሚለው የተከሣሽ ክርክር በፍ/ሕ/ቁጥር 2574/2/ የተመለከተው የ3ወር ደመወዝ ክፍያ የሥራ ውሉ ለተቋረጠበት እንጂ የሥራ ውሉ ለታገደበት ጊዜ የሚመለከት አይደለም በማለት ከሥ የቀረበበትን ገንዘብ ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍል ውሣኔ ሠጥቷል።

አመልካቹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙ ተሠርዞበታል።

አመልካቹ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ስላለበት ይታረምልኝ ሲል በ14/5/97 የተፃፈ የሠበር አቤቱታ አቅርቧል።

የአቤቱታው ፍሬ ቃል ተጠሪው በ5/10/95 እና በ5/2/95 ተፅፎ የተሠጣቸው ደብዳቤ የሥራ ስንብት ሣይሆን የሥራ ልምድ የምሥክር ወረቀት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በአግባቡ አልመረመረም።

አመልካች ተጠሪን ከሥራ ለማገድ ምክንያት ያደረገው በድርጅቱ ሥራና ገንዘብ ላይ በተለያዩ ጊዜያት ጉዳት ማድረሣቸውን የሚያመለክቱ

ናቸው፡፡ ፍ/ቤቱ የፍ/ህ/ቁጥር 2575 ስለሥራ ውል መቋረጥ እንጂ ስለ ሥራ ውል ማገድ የሚመለከት አይደለም ያለው ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪው በእገዳ ላይ ለቆዩበት ጊዜ ሥራ እንዳይሠሩ የከለከላቸው ድርጅቱ ነው ተብሎ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ሥህተት ነው ምክንያቱም የፍ/ሕ/ቁጥር 2540 ሥራ ላልተሠራባቸው ቀኖች ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም የሚለውን የሚቃረን ነው፡፡ የፍ/ህግ ቁጥር 2574/2/ ከ3ወር የማይበልጥ ክፍያ እንዲከፈል የደነገገው የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ ነው ተብሎ የተሠጠው ትርጉም ሥህተት ነው በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ስለሆነ ውሣኔዎቹ ተሽረው ወጭና ኪሣራ ተከፍሎን እንሠናበት የሚል ነው፡፡

የሠበረ አቤቱታ ማመልከቻው ለተጠሪው ደርሶ ሚያዝያ 19/1997 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የአመልካች የሠበር አቤቱታ የሕግ ሥህተት መፈፀሙን አይገልጽም፣ የ6ወር የጊዜ ገደብ የከሣሽን የጥቅም ጥያቄ በይርጋ አያግደውም፣ ተጠሪው በጥፋት ተከስሼ አላውቅም፣ ባልተቀጣሁበት ጉዳይ ጥፋት ነው ተብሎ ለሠበር አቤቱታ መቅረቡ

ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪ በ5/10/95 እና በ5/2/95 የተፃፈው የሥራ የምሥክር ወረቀት እንጂ የሥራ ሥንብት ደብዳቤ አይደለም ያሉት የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የህግ ሥህተት መሆኑን አያመለክትም፣ አመልካች መ/ቤት ከሥራና ከደመወዝ ያለበቂ ምክንያት አግደውና አሠናብተው ስለአጉላሉኝ በደሉ ታይቶ የተሠጠው ውሣኔ የሕግ ሥህተት ሣይሆን የፍሬ ነገር ክርክር ነው፣ በፍ/ሕግ.ቁጥር 2540 ሥራ ላልሠራባቸው ቀኖች ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም ለተባለው ተጠቃሹ ህግ ሠራተኛው ሥራውን በራሱ ፍላጐት ሣይሠራ ሲቀር እንጂ አሠሪው ሥራ ሲከለክለው የሚጠቀስ አይደለም፣ የፍ/ሕግ ቁጥር 2574/2/ ለኪሣራ እንጂ ውዝፍ ደመወዝን የሚመለከት አይደለም፣ ከዚህ ጉዳይ ጋርም ግንኙነት የለውም ስለሆነም ጥያቄው ከበቂ ኪሣራ ጋር ተሠርዞ እንድሠናበት በማለት ሲከራከር አመልካቹ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን፣ በኛ በኩል ተጠሪው ከሥራ ታግዶ ለቆየበት ጊዜ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አግባብ ካላቸው

ሕጐች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ተጠሪው በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የሥራ መሪ ሆኖ ሲሠራ የነበረ በመሆኑ የአመልካችና የተጠሪው የሥራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 16 የሥራ አገልግሎትን መስጠት ስለሚመለከቱ ውሎች ከቁጥር 2512 እና ተከታታይዎቹ በተደነገጉት ሕጐች መሠረት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሠሪን የሥራ ውል ስለማቋረጥ እንጂ አሠሪን ከሥራ ስለማገድ በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም ካለ በኂላ በፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ መሠረት አመልካቹ ተጠሪውን ከሥራና ከደመወዝ አግዶ ለቆመባቸው ወራቶች ደመወዙን ይክፈለው ሲል ወስኗል፡፡

በመሠረቱ ከፍ/ሕግ ቁጥር 2534 ድንጋጌ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ደመወዝ ለተሠራ ሥራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሠራ ሥራ የሚከፈል አይደለም፡፡

የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2540 ይህንኑ የሕጉን መርህ በመከተል ሥራ ላልተሠራባቸው ጊዜያት ወይም ቀናት ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም በማለት ግልጽ ድንጋጌ አስፍሮ ይገኛል፡፡

ይሁንና የፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ ሠራተኛው አንድም የሥራ አገልግሎት ባይሠጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሠሪው የሥራ ማይሠጠው በመቅረቱ ወይም እንዳይሠራ በመከልከሉ የተነሣ የሆነ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት አለው ሲል ሠራተኛው የሥራ ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሥራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሠሪው ሥራ ማይሠጠው ወይም እንዳይሠራ በከለከለው ጊዜ የሚያገለግል እንጂ ሠራተኛው ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ የሥራ አገልግሎት ላልሠጣባቸው ጊዜያት ደመወዝ እንዲከፈለው የሚፈቅድ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ብቻ ብለው በተመለከቱት የፍ/ብሔር ድንጋጌዎች አተረጓጐም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34240 በ5/5/97 የሠጠው ውሣኔ እና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ1119 በ1-2-97 የሠጠው ውሣኔ

በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት የተሻሩ ስለሆነ የውሣኔው ግልባጭ

ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረሣቸው መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡